የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN
COMMUNICATIONS AUTHORITY

# የቴሌኮሚኒኬሽን የብሔራዊ ሮሚንግ
# የጅምላ ሽያጭ መመሪያ
# ቁጥር 800/2013

ሐምሌ 2013 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# <u>የቴሌኮሙኒኬሽን የብሔራዊ ሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት መመሪያ</u>

በቴሌኮሙኒኬሽኖች ኦፐሬተሮች መካከል የብሔራዊ ሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት ስምምነቶችን ማስተዳደር የሚያስችል ማዕቀፍ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የቴሌኮሙኒኬሽን የብሔራዊ ሮሚንግ አገልግሎት ስምምነቶችን ለማስተዳደር የሚያስችሉ የህግ እና የአሰራር ስርዓቶች ላይ ግልጽነት መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት፤

በመጀመሪያ የኔትዎርክ ትግበራ ወቅት አዳዲስ ባለፍቃዶች የሴሉላር የሞባይል ሽፋን በሌላቸው ቦታዎች ላይ ደንበኞችን መድረስ የሚችሉበትን ምቹ የስራ ከባባዊ ሁኔታን መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሮች መካከል ውድድርን ከፍ ለማድረግ የመግቢያ እና የማስፋፊያ ገደቦችን ዝቅ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በማመን፤

በኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 አንቀጽ 6(2) ፣ 44(7) እና 54(2) መሰረት ባለስልጣኑ ይህንን የቴሌኮሙኒኬሽን የብሔራዊ ሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት መመሪያን አውጥቷል።

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የቴሌኮሙኒኬሽን የብሔራዊ ሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ መመሪያ ቁጥር 800/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1) **"ባለሥልጣን"** ማለት በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ነው፤

2) **"ታችኛ ክወና"** ማለት የችርቻሮ አገልግሎት የሚሰጥ እና ተዋራዳዊ በሆነ መልኩ የተደራጀ ኦፐሬተር የንግድ ስራ ሲሆን የችርቻሮ ንግድ አቅርቦቱን ሲያከናውን በህግ የተለየ እና ራሱን የቻለ ሌላ ተቋም ስራውን በሚሰራበት መልክ ነው።

3) **"የመሠረተ ልማት መጋራት"** ማለት በተዋዋዮቹ መካከል የሚደረገው ስምምነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመሰረተ ልማት እና የኮሎኬሽን አቅራቢ ከመሰረተልማት እና ኮሎኬሽን ፈላጊ ጋር ቋሚ እና ገባሪ

መሠረተ ልማቶችን የሚጋሩበት የተለያየ አሰራር ሲሆን የኔትወርክ ክፍሎችን፣ ሥርዓቶችን፣ መሣሪያዎችን፣ አገልግሎቶችን፣ ቅጥር ግቢዎችን ወይም የመጠቀም መብቶችን ጨምሮ ሌሎችንም ያካትታል፤

4) **የህዳግ ጥበት**" ማለት አግባብነት ባለው የችርቻሮ ገበያ ውስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፐሬተር የችርቻሮ ንግድ ውስጥ ላሉ ሌሎች ተወዳዳሪ የቴሌኮም ኦፐሬተሮች የጅምላ ሽያጭ በማከናወን የችርቻሮ ዋጋን እና የጅምላን ዋጋ ሲወስን እና ባስቀመጠው የጅምላ እና የችርቻሮ ዋጋ መካከል ያለው የዋጋ ልዩነት በችርቻሮ ንግድ ውስጥ ያለ የተሻለ አፈጻጸም እና ውጤታማ የሆነ ተወዳዳሪ አገልግሎት እየሰጠ ውድድር ውስጥ መቆየት የማያስችለው ሁኔታ ሲከሰት የሚፈጠር ነው::

5) **"የሞባይል የኮሚዩኒኬሽን አገልግሎቶች"** ማለት ተጠቃሚዎች የድምጽ ጥሪ ፥ አጭር የጽሁፍ መልክት እንዲሁም ዳታ ወይም ሌሎች የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን መላክ እና መቀበል እንዲችሉ ፈቃድ በተሰጠው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሮች የሚሰጥ የኮመኒኬሽን አገልግሎት ነው::

6) **"ብሔራዊ ሮሚንግ"** ማለት አንድ ተጠቃሚ አገልግሎት ከሚሰጠው አገልግሎት ሰጪ ጂኦግራፊያዊ ሽፋን ክልል ውጭ በሚንዝበት ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የሌላ አገልግሎት ሰጪ ኔትዎርክን በመጠቀም ራስ መር በሆነ መልኩ የድምጽ ጥሪ የማድረግ እና የመቀበል፥ አጭር መልክት እና ዳታን የመላክ እና የመቀበል ወይም ሌሎች አገልግሎቶችን ማግኘት የሚችልበት መንገድ ነው::

7) **"የብሔራዊ ሮሚንግ የሽፋን ቦታ"** ማለት ጥቅል የብሔራዊ ሮሚንግ አገልግሎቶች ሊሰጥበት የሚገባ ወይም የሚሰጥበት ጂኦግራፊያዊ አካባቢ ነው::

8) **"የብሔራዊ ሮሚንግ ዘመን"** ማለት  አዲስ ፈቃድ ያለው ኦፐሬተር  የሞባይል ተደራሽነት እና የጥሪ መነሻዎች በተመለከተ አግባብነት ባለው ገበያ ውስጥ ጉልህ የገቢያ ድርሻ  ካለው ኦፐሬተር የጅምላ ብሔራዊ ሮሚንግ   ሽያጭን መጠየቅ የሚችልበት የጊዜ ገደብ ነው::

9) **"አዲስ ባለ ፈቃድ"** ማለት በቴሌኮሙኒኬሽን ፈቃድ መመሪያ ቁጥር 1/2013 መሠረት ባለሥልጣኑ ፈቃድ የሰጠው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር ማለት ሲሆን፣ ይህ የቀድሞውን ኦፐሬተር አይጨምርም::

10) **"የአቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ"** ማለት የጅምላ ብሔራዊ ሮሚንግ አገልግሎት ስምምነትን የተመለከተ መደበኛ ቅጽ ሲሆን በተለያዩ ክፍል የተከፈሉ አግባብነት ያላቸው የሚሰጡ አገልግሎቶችን እና ክፍያን ጨምሮ ተንዳኝ ህጎችን እና ሁኔታዎችን የሚገልጽ ሰነድ ነው::

11) **“የችርቻሮ አገልግሎት”** ማለት ለመጨረሻ ተጠቃሚው ወይም ለደንበኛ የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን ለቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጥ አገልግሎትን አያካትትም፡፡

12) **“የሮሚንግ’ አቅራቢ”** ማለት አዲስ ፈቃድ ባለው ኦፐሬተር የጅምላ የሮሚንግ ሽያጭ እንዲያከናውን ጥያቄ የሚቀርብለት ወይም የጅምላ አገልግሎቱን እየሰጠ ያለ ኦፐሬተር ነው፡፡

13) **“የሮሚንግ ጠያቂ”** ማለት ከሌላ የቴሌኮሙዩኒኬሽን ኦፐሬተር ‘የጅምላ የሮሚንግ ሽያጭ የሚጠይቅ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር ነው፡፡

14) **“አገልግሎት ሰጭ”** ማለት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚሰጥ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር ማለት ነው፡፡

15) **“ጉልህ የገቢያ ድርሻ”** ማለት ለኮመኒኬሽን አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ መገልገያዎችን ወይም በገበያ ውስጥ ያለውን ድርሻ አቅም በመጠቀም በኮመኒኬሽን አገልግሎት ዋጋ ወይም አቅርቦት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የማሳረፍ ችሎታ ነው፤

16) **“ተገልጋይ”** ማለት ለተወሰነ ግዜ ከቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር ጋር ስምምነት ውስጥ በመግባት ወይም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሩ ያስቀመጠውን ሁኔታዎች በመቀበል የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች የሚያገኝ እና ለዚህም ተገቢነት ያለውን ክፍያ የሚከፈል ማንኛውም ሰው ነው፡፡

17) **“በተዋረድ የተቀናጀ ኦፐሬተር”** ማለት የችርቻሮ እና የጅምላ አገልግሎቶችን የሚያቀርብ የቴሊኮምኒኬሽን ኦፐሬተር ነው፡፡

18) **“ብሔራዊ የሮሚንግ አገልግሎት የጅምላ ሽያጭ”** ማለት መሰረተ ልማት የማጋራት አገልግሎት ዓይነት ሲሆን የሞባይል ተደራሽነት አቅርቦትን እንዲሁም የጥሪ መነሻን ከኦፐሬተሩ የሞባይል ሴሉላር ኔትዎርክ ለታችኛው ክዋና ወይም አገልግሎቱ በሚሰጥበት ቦታ ላይ የሞባይል ሴሉላር ሽፋን ለሌለው ኦፐሬተር የሚሰጥ አገልግሎት ነው፡፡ይህ አገልግሎት የሞባይል ደራሽነት እና የጥሪ መነሻ የጅምላ ሽያጭ ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

19) **“የሥራ ቀናት”** ማለት ስራ የሚሰራባቸው ቀናት ብቻ ሲሆኑ ቅዳሜ፣ እሁድ  እና ማናቸውንም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ የበዓላት ቀን የተባለ ነው፡፡

## 3. <u>ዓላማ</u>

የዚህ መመሪያ ዋነኛ ዓላማዎች፦

1) በቴሌኮሙኒኬሽኖች ኦፐሬተሮች መካከል የብሔራዊ ሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት ስምምነቶችን ማስተዳደር የሚያስችል ማዕቀፍ ማቅረብ፤

2) በአዋጁ አንቀጽ 44 መሠረት ባለሥልጣኑ ብሔራዊ ሮሚንግ አገልግሎት ስምምነቶችን ለማስተዳደር ሊከተላቸው የሚገቡ ህግ እና የአሰራር ስርዓቶች ላይ ግልጽነት መፍጠር፤

3) በመጀመሪያ የኔትዎርክ ትግበራ ወቅት አዳዲስ ባለፍቃዶች የሴሉላር የሞባይል ሽፋን በሌላቸው ቦታዎች ላይ ደንበኞችን መድረስ የሚችሉበትን ምቹ የስራ ከባባዊ ሁኔታን መፍጠር እና

4) በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሮች መካከል ውድድርን ከፍ ለማድረግ የመግቢያ እና የመስፋፊያ ገደቦችን ዝቅ ማድረግ።

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

1) ይህ መመሪያ በኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ወሰን ውስጥ የብሄራዊ ሮሚንግ ጅምላ ሽያጭ አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ ተፈጻሚ ይሆናል።

2) የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች በተፈጥሮ አደጋ ፥ በታቀድ ወይም ባለታቀደ የኔትዎርክ መቆራረጥ ምክንያት የቴሌኮመኒኬሽን አገልግሎት እንዳይቆረጥ በማሰብ በኦፐሬተሮች መካከል በሚመሰረቱ የብሄራዊ ሮሚንግ ጅምላ ሽያጭ አገልግሎቶች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

# ክፍል ሁለት
# የባለስልጣኑ ሚና

## 5. የባለስልጣኑ ሚና

1) ባለሥልጣኑ -

ሀ) ብሔራዊ ሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎትን ይቆጣጠራል፤

ለ) በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሮች መካከል የሚኖር የብሔራዊ ሮሚንግ የጅምላ ሽያጭን በሚመለከቱ ደንጋጌዎች ላይ ከፍተኛ መተማመንን ይፈጥራል;

ሐ) ተዋዋይ ወገኖች ብሄራዊ ሮሚንግ የጅምላ ሽያጭን በተመለከተ ስምምነት ላይ መድረስ በማይችሉበት ጊዜ በአዋጁ አንቀጽ 44 (9) እና በዚህ መመሪያ መሠረት የስምምነቱን ውሎች ለመወሰን ጣልቃ ይገባል ፤ እና

መ) የብሄራዊ ሮሚንግ ጅምላ ሽያጭ ስምምነቶች አግባብነት ካላቸው ፈቃዶች እና ከዚህ መመሪያ ወይም ባለሥልጣኑ ካጸደቀው እና ተፈጻሚነት ከሆነ መመሪያ ጋር አብሮ መሄድ መቻሉን በማንኛውም ጊዜ ይመረምራል።

2) ባለሥልጣኑ ፦

ሀ) በራሱ ወይም ከተዋዋይ አካላት በአንዱ ጠያቂነት ጣልቃ በመግባት የብሄራዊ ሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት ክፍያ በአዋጁ አንቀጽ 45 እና 46፥ በዚህ መመሪያ ወይም በባለስልጣኑ በጸደቀ

እና ተፈጻሚነት ባለው ማንኛውም መመሪያ መሰረት ህጋዊ መሆን እና አለመሆኑን ይወስናል፤ እና

ለ) በራሱ ወይም በተዋዋይ አካል በአንዱ ጠያቂነት ጣልቃ በመግባት በዚህ መመሪያ አለመግባባት መፍቻን አስመልክቷ በተቀመጡ መንገዶች ወይም በባለስልጣኑ የአለመግባቢያ መፍቻ መመሪያ መሰረት የብሄራዊ ሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎትን በተመለከተ የተነሱ አለመግባባቶችን ይፈታል፤

## ክፍል ሶስት
## የብሔራዊ ሮሚንግ የጅምላ አገልግሎቶች አጠቃላይ መርሆዎች

## 6. የብሔራዊ ሮሚንግ የጅምላ አገልግሎቶች አጠቃላይ መርሆዎች

1) ሁሉም የብሄራዊ ሮሚንግ የጅምላ ስምምነቶች ከአጠቃላይ የግልጽነት ፣ አድልዎ አለማድረግ እና ህጋዊ ታሪፍ መርሆች ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው፡፡

### ሀ) ግልጽነት

i. ባለሥልጣኑ ከብሄራዊ ሮሚንግ ጅምላ ሽያጭ ጋር የተያያዙ ውሳኔዎችን ለመስጠት የሚያልፍባቸው ሂደቶች የሚታዩ እና ግልፅ መሆን አለባቸው፡፡

ii. አግብብነት ባለው ገበያ ውስጥ የሞባይል ተደራሽነት ጅምላ ሽያጭ እና የጥሪ መነሻ አገልግሎትን በተመለከተ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው የተወሰነ ኦፕሬተር በባለስልጣኑ የጸደቀውን የብሄራዊ ሮሚንግ ጅምላ ሽያጭ አቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ እንዲታተም ማድረግ አለበት፡፡

iii. ባለሥልጣኑ የጸደቀውን የብሄራዊ ሮሚንግ ጅምላ ሽያጭ አቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ በደረ ገጹ ላይ እንዲወጣ ያደርጋል እንዲሁም የሮሚንግ አቅራቢው ለሮሚንግ አገልግሎት ፈላጊ ያለ ክፍያ ተደራሽ ያደርጋል፡፡

### ለ) አድልዎ አለማድረግ

የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት አቅራቢ የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት አቅርቦት የውል ቃሎችና ሁኔታዎች ለራሱ ታችኛ ክወና ወይም ለሌላ ኦፕሬተር ከሚያቀርብበት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው፡፡

### ሐ) ህጋዊ ታሪፍ

ለሮሚንግ ጅምላ ሽያጭ አገልግሎት የሚውሉ ታሪፎች በአዋጁ አንቀጽ 45 ፣ በዚህ መመሪያ እና የቴሌኮመኒኬሽን ህጋዊ ታሪፍን ጨምሮ በባለሥልጣኑ በጸደቁ እና ተግባር ላይ ባዋሉ ሌሎች መመሪያዎች መሰረት ህጋዊ መሆን አለባቸው፡፡

2) የሮሚንግ የጅምላ አገልግሎት አዲስ ፈቃድ ያለው ኦፕሬተር ተገልጋይ አገልግሎት የሚሰጠው ኦፕሬተር የሞባይል ኔትዎርክ ሽፋን በሌለበት ቦታዎች ላይ የሞባይል ኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች እንዲያገኝ ያስችለዋል፡፡ ይህ አገልግሎት ተገልጋዩ የራሱ ኦፕሬተር ሽፍን ባለባቸው አካባቢዎች ላይ ከሚያገኛቸው አገልግሎቶች ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው፡፡

7. <u>ብሔራዊ የሮሚንግ አገልግሎት ጊዜ</u>

1) የሮሚንግ ጅምላ ሽያጭ አገልግሎት አዲስ ፈቃድ ላለው ኦፕሬተር የንግድ ስራውን መጀመሩን ይፋ ከተደረገበት ቀን ጅምር ባሉ ሰላሳ ስድስት (36)ወራት ግዚያት ውስጥ የሚሰጥ ይሆናል፤

2) ተዋዋይ ወገኖች ሲስማሙ እና ባለሥልጣኑ ስምምነቱን ሲያጸድቀው አዲስ ፈቃድ ላለው ኦፕሬተር የሚሰጠው የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት የቆይታ ዘመን ከሠላሳ ስድስት (36) ወራት በላይ ሊራዘም ይችላል፡፡

8. <u>የብሔራዊ ሮሚንግ አገልግሎ ሽፋን ቦታ</u>

1) የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት በአግባቡ ተለይተው በተከለሉ ጂኦግራፊያዊ ቦታዎች ላይ ሲሆን አዲስ ፈቃድ ያለው ኦፕሬተር የራሱን የሞባይል ኔትወርክ የዘረጋበት እና አገልግሎት የሚሰጥበትን ቦታዎች አያካትም፤

2) የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት እያገኘ ያለ አዲስ ባለፍቃድ በብሄራዊ ሮሚንግ አማካኝነት የሚያገኘው አገልግሎትን በፈቃዱ ላይ ለተመለከተው የኔትዎርክ ማስፋፊያ ወይም ሽፋን ግዴታ መውጫ ተደርጎ ይቆጠርልኝ ማለት አይችልም፤

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ብሄራዊ የሮሚንግ ጅምላ ሽያጭ አገልግሎቶች የአሰራር ስርዓት</u>

9. <u>መብቶች እና ግዴታዎች</u>

1) አዲስ ፈቃድ ያለው ኦፕሬተር በባለሥልጣኑ የሞባይል ጅምላ ሽያጭ ተደራሽነት እና የጥሪ መነሻ በተመለከተ አግባብነት ባለው ገበያ ውስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው ከወሰነው ከማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሮሚንግ ጅምላ ሽያጭ አገልግሎቶችን በብሔራዊ ሮሚንግ የቆይታ ጊዜ ውስጥ የመጠየቅ መብት አለው፡፡

2) በባለሥልጣኑ የሞባይል ጅምላ ሽያጭ ተደራሽነት እና ጥሪ መነሻ ላይ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው የተወሰነ እና በአዲስ ባለፈቃድ የሮሚንግ ጅምላ ሽያጭ አገልግሎት ጥያቄ የቀረበለት

የሮሚንግ አቅራቢ፤ የቀረበው ጥያቄ ቴክኒካዊ በሆነ መንገድ መመለስ እስከተቻለ ድረስ መመለስ እና አገልግሎቱን በተመለከተ በቅን ልቦና እና ምክንያታዊ በሆኑ ደንብ እና ሁኔታዎች መደራደር አለበት።

3) የሮሚንግ አቅራቢ የተጠየቀውን የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ጥያቄን፡-

ሀ) በቴክኒክ ምክንያት

i. አለመጣጣም ከተፈጠረ; ወይም

ii. ለቴሌኮሙኒኬሽን ኔትዎርክ ወይም አገልግሎቶች ደህንነት ፣ አስተማማኝነት ፣ ምሉሁነት እና ደህንነት ምክንያታዊ ያልሆነ ከፍተኛ ስጋት ከፈጠረ ፤ ወይም

ለ) የሮሚንግ አገልግሎት ፈላጊው የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት መጠየቂያ ጊዜ ካበቃ ፤ ወይም

ሐ) የሮሚንግ አገልግሎት ፈላጊው የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት ጥያቄ በጠየቀበት አካባቢ ላይ የራሱን የሞባይል ኔትወርክ ከዘረጋ፤

ውድቅ የማድረግ መብት ይኖረዋል፡

## 10.<u>በቅን ልቦና ድርድር ስለማድረግ</u>

1) የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ስምምነት ድርድር በኦፐሬተሮች መካከል በቅን ልቦና መካሄድ አለበት። ከሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ጋር የተያያዙ አለመግባባቶች የተከሰቱ እንደሆነ አለመግባባቶችን በሙሉ ለመፍታት ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለባቸው።

2) በቅን ልቦና በሚደረጉ ድርድሮች ላይ እያንዳንዱ ተደራዳሪ ፤-

ሀ) ሌላኛውን ወገን ሆን ብሎ ማሳሳት፤

ለ) ሌላኛውን ወገን በኃይል ወይም በመጫን ስምምነት ላይ እንዲደርስ ማስገደድ፤ ወይም

ሐ) ሆን ተብሎ ድርድሮችን ማደናቀፍ፤ የለበትም።

3) የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም በቅን ልቦና የመደራደር መርሆዎችን እንደመጣስ ያስቆጥራል፤

ሀ) ለሌላው የቴሌኮመኒኬሽን ኦፕሬተር ተገቢነት ያላቸውን ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎችን በወቅቱ አለመስጠት፤

ለ) ጫና የሚያሳድሩ ወይም ያለአግባብ የተለጠጡ ወይም ገደብ የሚጥሉ ሚስጥርን ያለመግለጽ ስምምነቶችን እንዲፈረም መጠየቅ፤

ሐ) ለወደፊት ማሻሻያዎችን ለማድረግ የሚፈቅድ ድንጋጌ በስምምነት ውስጥ እንዲካተት አለመፍቀድ፤

መ) በስምምነቱ ውስጥ የተካተቱትን የውል ቃሎች እና ሁኔታዎችን ከጉዳዩ ጋር የማይዛመዱ ጉዳዮችን አልባት ከመስጠት ጋር ለማያያዝ መሞከር፤

ሠ) ወጪን መሰረት ያላደረገ ክፍያን መጠየቅ፤

ረ) ምክንያታዊ ያልሆኑ ደንቦች እና ሁኔታዎችን ማቅረብ፤

ሰ) ገዥ ውሳኔዎችን ለመፈጸም ሥልጣን ያለውን ሰው ለመሰየም በተደጋጋሚ ፈቃደኛ አለመሆንን ጨምሮ እና በዚህም ሳይወሰን ድርድርን የማዘግየት ድርጊቶችን መፈጸም፤ ፣ እና

ሸ) በባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚወስነው መሠረት በቅን ልቦና የመደራደርን መርህ ይጥሳሉ ብሎ ሊቆጥራቸው የሚችላቸውን ሌሎች ደርጊቶች መፈጸም፡፡

## 11.<u>የብሔራዊ የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎቶችን ስለመጠየቅ</u>

1) አንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ጥያቄን ለሌላ ኦፐሬተር ሲያቀርብ ጥያቄውን በሚከተለው መልክ ያቀርባል፤

ሀ) በጽሑፍ ለሮሚንግ አቅራቢ ማቅረብ፣

ለ) ስለተፈለገው የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት ዓይነት በቂ ኢንፎርሜሽን፤ ድርድሩን ለመጀመር የታሰበበትን ቀን፣ የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት የሚፈለግበትን ቀን፥ የብሄራዊ ሮሚንግ የሚሸፍነው ቦታ፥ የሮሚንግ ጠያቂው የብሄራዊ የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ የመጠየቂያ ግዜ ማብቂያ እና የቴክኒክ መስፈርቶችን ጨምሮ እና በእነዚህም ሳይወሰን ከተጠየቀው የአገልግሎት ዓይነት ጋር የተያያዙ የተሟሉ መረጃዎችን ማካተተ፤ እና

ሐ) ስለአቀረበው ጥያቄ በአምስት (5) የሥራቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ፡፡

2) የሮሚንግ አቅራቢ የሮሚንግ ፈላጊ ጥያቄ በደረሰው በአስር (10) የስራ ቀናት ውስጥ፦

ሀ) ከተጠየቀው የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት አገልግሎት ጋር የተያያዙ ደርድሮችን በታቀደው ቀን መጀመር፤

ለ) የተጠየቀውን የሮሚንግ አገልግሎት ዓይነት ማቅረብ፤ እና

ሐ) በሮሚንግ ጠያቂ የግዜ ሰሌዳ ውስጥ የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት መስጠት ፤ መቻል ወይም አለመቻሉን ለሮሚንግ ፈላጊው በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል።

3) የሮሚንግ አገልግሎት አቅራቢው ለሮሚንግ አገልግሎት ፈላጊው የተጠየቀውን የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት መስጠት መቻሉን በሚያሳወቅበት ግዜ፣ ከተገኝ የጸደቀውን የአቅርቦት መነሻ ሰነድ ቅጂን መስጠት እና የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት ጥያቄ ከተቀበለ ከአስራ አምስት (15) የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ድርድር መጀመር አለበት።

4) የሮሚንግ አገልግሎት አቅራቢ እና የሮሚንግ አገልግሎት ፈላጊ በቅን ልቦና መደራደርና ድርድሩን ለማጠናቀቅ የሚቻላቸውን ሁሉ ጥረት በማድረግ ድርድሩ በተጀመረ ከሰላሳ (30) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወይም ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በተስማሙበት ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መፈራረም ይኖርባቸዋል።

5) የሮሚንግ አገልግሎት አቅራቢ እና የሮሚንግ አገልግሎት ፈላጊ የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ስምምነት ለመተግበር የሚያስችሉ የኔትዎርክ መሰረተልማት ሁኔታዎችን ስምምነቱ በተፈረመ ከሠላሳ (30) የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወይም ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በተስማሙበት ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መጠናቀቃቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡ ፡

6) የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ጥያቄ ወድቅ የሚሆነው በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 9(3) በተዘረዘሩት ምክንያቶች ብቻ ሲሆን የሮሚንግ አቅራቢ ጥያቄውን ውድቅ ያደረገበት አሳማኝ ምክንያትን የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት ጥያቄን በተቀበለ ከአስር (10) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በጽሑፍ መግለጽ ይኖርበታል።

7) የሮሚንግ አቅራቢው የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ጥያቄን ውድቅ የተደረገበትን ቅጂ ለሮሚንግ ፈላጊው በደረሰው ከሰባት (7) የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በባለሥልጣኑ ፋይል ውስጥ እንዲያያዝ ማድረግ ይኖርበታል።

8) በአዋጁ አንቀጽ 44(9) መሠረት ተዋዋይ ወገኖቹ ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ከተዋዋዮቹ አንዱ ለባለሥልጣኑ ይግባኝ ማቅረብ ወይም ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት ጣልቃ በመግባት በአዋጁ አንቀጽ 34 እና ከአንቀጽ 36 እስከ 38 ወይም ሙግትን ለመፍታት በወጣው መመሪያ መሠረት አስገዳጅ ውሳኔ መስጠት ይችላል።

## ክፍል አምስት

## የ ብሔራዊ ሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት ስምምነቶች

### 12.የብሔራዊ ሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት ስምምነቶች

1) ሁሉም የሮሚንግ ጅምላ ሽያጭ ስምምነቶች በጽሑፍ ሆነው፤

   ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 (1) የተደነገገውን መርሆዎች የተከተሉ፣

   ለ) በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ፈቃዶች የተመለከቱትን የውል ቃሎችን እና ሁኔታዎችን የሚያከብሩ፣

   ሐ) በኢንዱስትሪው በስፋት ተቀባይነት ያገኙ ወይም በባለሥልጣኑ የፀደቁ ደረጃዎችን የሚያሟሉ፤ እና

   መ) ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ እና በባለሥልጣኑ ከወጣ ተፈጻሚነት ካለው ማናቸውም መመሪያ ጋር የተጣጣመ፤ መሆን ይኖርበታል።

2) የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ስምምነት የሮሚንግ ፈላጊ በህግ መሠረት መስጠት የሚችለውን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ድንጋጌን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገደብ ወይም እንዳይፈጸም የሚያደርግ መሆን የለበትም።

### 13.የብሔራዊ ሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት ስምምነቶች ፋይል ስለማድረግ

1) የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አቅራቢ የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ስምምነት ቅጂን ስምምነቱ በተፈረመ ከሰባት (7) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በባለሥልጣኑ ፋይል እንዲያያዝ ማድረግ አለበት።

2) ባለሥልጣኑ በተያያዘው የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ስምምነት ውስጥ የተካተቱትን የውል ቃሎች እና ሁኔታዎችን መገምገም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በራሱ ሥልጣን ከተዋዋይ ወገኖቹ ከአንዱ ተጨማሪ መረጃዎች መጠየቅ ይችላል።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ባለስልጣኑ ሰነዱን እንዲያጸድቅ ጥያቄ በቀረበለት በሃያ (20) የስራ ቀናት ውስጥ የሚከተሉትን ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፦ ፤

   ሀ) የቀረበውን ስምምነት ማጽደቅ ፣ ወይም

   ለ) የቀረበውን ስምምነት ውድቅ ማድረግ እና ለዚህም ምክንያት የሆኑውን ነጥብ በጹሁፍ ለሮሚንግ አቅራቢው ማሳወቅ ወይም

   ሐ) የቀረበው የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት ስምምነት በአዋጁ አንቀፅ 44 እና 45 ፣ በዚህ መመርያ እና ባለሥልጣኑ ባጸደቀው በማንኛውም አግባብ ባለው መመሪያ

መሰረት የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ የቁጥጥር ሂደት ለመጀመር ማሰቡን ይገልጻል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የቁጥጥር ሥራ በአዋጁ ከአንቀጽ 35 እስከ 38 የተመለከቱትን አሰራሮች ወይም ባለሥልጣኑ ያፀደቀውን ማንኛውንም መመሪያ በተከተለ መልኩ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

4) ባለሥልጣኑ እንዲጸድቅለት የቀረበለትን ስምምነት በሃያ (20) የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልሰጠበት፡ ስምምነቱ እንደፀደቀ ይቆጠራል ፡፡

5) ባለሥልጣኑ የሁለቱንም ወገኖች ለንግድ ስጋት ተጋላጭ የሆኑ መረጃዎች ሚስጥራዊነት በጠበቀ መልኩ የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ስምምነቶችን በድረ ገፁ ላይ ማውጣት ይችላል፡፡ ባለስልጣኑ ይህን ተግባር ሲያከናውን የመረጃዎችን ሚስጥራዊነት ለማረጋገጥ ምክንያታዊ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 14.<u>የብሔራዊ ሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት ስምምነቶችን ስለማሻሻል</u>

1) ፋይል የተደረገው የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ስምምነትን ተዋዋይ የሆኑ ወገኖች ስምምነቱ ላይ ያሉ ሁኔታዎች እና የባለስልጣኑ ፈቃድ መሰረት በማድረግ በጋራ ማሻሻል ወይም ማስተካከል ይችላሉ፡፡ የተሻሻለው ወይም የተስተካከለው ስምምነት በተፈረመ ከሰባት (7) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከባለሥልጣኑ ፋይል ጋር መያያዝ አለበት፡፡

2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13(1) መሠረት ፋይል የተደረገው የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ስምምነት ተዋዋይ የሆኑ ወገኖች ስምምነቱን በሚያሻሽሉት ወቅት የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች ላይ መስማማት ያልቻሉ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ከተዋዋይ ወገኖቹ በአንዱ ጥያቄ ወይም በራሱ ሥልጣን ጣልቃ በመግባት አለመግባባትን ለመፍታት በወጣው መመሪያ መሠረት የውል ቃሎችን ወይም ሁኔታዎችን መወሰን ይችላል፡፡

## 15.<u>የብሄራዊ የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ስምምነት ስለመቋረጥ</u>

1) የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ስምምነት የሚቋረጠው በስምምነቱ የተመለከቱትን የውል ቃሎች በጥብቅ በመከተል ነው፡፡

2) በባለስልጣኑ ዘንድ የተያያዘን የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ስምምነትን ማቋረጥ የፈለገ ተዋዋይ ወገን የውሉን ማቋረጫ ምክንያቶች በመጥቀስ ለሌላው ወገን ከስልሣ (60) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜ መሥጠት እና በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

3) የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ስምምነት ጥሰት በሚኖርበት ወቅት ማስጠንቀቂያ ሰጪው ኦፕሬተር ለሌላው ተዋዋይ ወገን ጥሰቱን እንዲያስተካክል ከሠላሣ (30) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ማስጠንቀቂያ የደረሰው ወገን ጥሰቱን ካላስተካከለ

ማስታወቂያ የሰጠው ወገን ስምምነቱን ያቋርጣል ወይም በባለሥልጣኑ ሙጉት መፍቻ መመሪያ መሠረት ጣልቃ እንዲገባ መጠየቅ ይችላል፡፡

4) የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ስምምነት የተቋረጠበት ተዋዋይ አካል ባለሥልጣኑ ጣልቃ እንዲገባ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ በዚህ ግዜ ባለስልጣኑ የሙጉት መፍቻ መመሪያን መሠረት በማድረግ ጣልቃ ይገባል፡፡

5) የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አቅራቢ የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ስምምነቱን ካቋረጠ፤ ይህኑ በተመለከተ ለባለስልጣኑ በጽሁፍ ከ 7 (ሰባት) የስራ ቀናት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ማሳወቅ እና ስምምነቱ ያቋረጠበት ማስታወቅያ ቅጂን ማቅረብ አለበት፡፡

## 16. <u>የብሔራዊ የሮሚንግ የጅምላ የሽያጭ ማጣቀሻ ሰነድ</u>

1) በባለስልጣኑ አግባብነት ባለው ገበያ ውስጥ የሞባይል የጅምላ ሽያጭ ደራሽነት እና የጥሪ መነሻ አገልግሎትን በተመለከተ ጉልህ የገበያ ድርሻ አላቸው የተባሉ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተሮች የማጣቀሻ ሰነዳቸው እንዲጸድቅላቸው ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለባቸው፡፡ ይህ የማጣቀሻ ሰነድ ባለስልጣኑ እንዲቀርብለት ትህዛዝ ከሰጠበት ከሰላሳ (30) በማይበልጥ የስራ ቀናት ውስጥ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

2) የማጣቃሻ አቅርቦት ሰነዱ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎችን ማካተት እና ከ ድንጋጌዎቹ ጋር መጣጣም አለበት፤

3) ባለሥልጣኑ የቀረበለትን የአቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድን ለመገምገም እና ለህትመት ብቁ መሆኑ አለመሆኑን ለመወሰን ወይም በቀረበው ሰነድ የተካተቱትን የውል ቃሎች ወይም ሁኔታዎች ጣልቃ በመግባት ለማሻሻል ከሃያ (20) የስራ ቀናት የበለጠ ጊዜ መውሰድ የለበትም፡፡ ባለሥልጣኑ እንዲጸድቅ የቀረበውን የአቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ በሃያ (20) የስራ ቀናት ውስጥ ውድቅ ካላደረገው ወይም ጣልቃ በመግባት ካልቀየረው የቀረበው ሰነድ እንደፀደቀ ይቆጠራል፡
፡

4) በባለሥልጣኑ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር፣ የጸደቀ የአቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ እስኪሻሻል ድረስ ፀንቶ ይቆያል፡፡ የፀደቀ የአቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ በባለሥልጣኑ ድረ ገጽ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

5) የፀደቀ የአቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ ያለው የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አቅራቢ ያሻሻለውን የአቅርቦት ማጣቀሻ ሰነዱ እንዲፀድቅለት በባለሥልጣኑ ዘንድ ሰነዱን ካሻሻለበት ቀን ጀምሮ ከሰባት (7) የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ፋይል ማድረግ አለበት፡፡

6) ባለሥልጣኑ የተሻሻለውን የአቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ በመገምገም ሊጸድቅ እና ለህትመት ብቁ መሆን አለመሆኑን በአስራ አምስት (15) የስራ ቀናት ውስጥ መወሰን ይኖርበታል፡፡ ባለሥልጣኑ እንዲጸድቅ የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ካላደረገው ወይም ሰነዱን በአስራ አምስት (15) የስራ ቀናት ውስጥ ጣልቃ ገብቶ ካላሻሻለው የተሻሻለው የደራሽነት ማጣቀሻ ሰነድ እንደፀደቀ ይቆጠራል፡፡

7) ባለሥልጣኑ እርሱ ዘንድ ፋይል የተደረገውን ወይም የፀደቀውን የአቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ፤ የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲኖሩ፦

ሀ) ፣የአቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ ወይም የሰነዱ ማናቸውም ድንጋጌ ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ ወይም በባለሥልጣኑ ከፀደቀ ተፈጻሚነት ካለው ማናቸውም መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ ወይም

ለ) ባለሥልጣኑ ጣልቃ መግባቱ ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው፤

በራሱ ሥልጣን ወይም ከቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የቀረበን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ጣልቃ በመግባት ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

8) ባለሥልጣኑ በእርሱ ዘንድ ፋይል የተደረገውን ወይም የፀደቀውን የአቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ ለማሻሻል ጣልቃ ለመግባት ከወሰነ በአዋጁ አንቀጽ 36 እና አንቀጽ 37 መሠረት እና ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሥነ-ስራዓቶችን በመከተል ተገቢ የሆኑትን መሻሻያዎች ግልጽ በሆነ መንገድ ማድረግ ይኖርበታል፤

ሀ) መደበኛ የአሠራር ሂደትን በመከተል የአቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድን ለማሻሻል መዘጋጀቱን ለሕዝብ ማስታወቂያ በማውጣት በጉዳዩ ያገባኛል ለሚሉ ወገኖች ያሳውቃል፡፡ ማስታወቂያውም የትኛው ድንጋጌ እንደሚሻሻልና ለምን እንደሚሻሻል የሚያሳይ ግልጽ የሆነ መግለጫ የያዘ ሆኖ ሰነዱ፤

i. በአዋጁ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን መሆኑን፤
ii. ከዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር የሚጋጭ መሆኑን፤
iii. በባለሥልጣኑ በፀደቀ ተፈጻሚነት ባለው መመሪያ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን መሆኑን፤ ወይም
iv. የሕዝብን ጥቅም የማያስጠብቅ መሆኑን፤

ማሳየት ይኖርበታል፡፡

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 (ሀ) የተጠቀሰው የሕዝብ ማስታወቂያው በማሻሻያነት የቀረበውን ሃሣብ እና የማሻሻያውን አሳማኝ ምክንያቶች ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሐ) ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች በማሻሻያ ሃሣቡ ላይ ምላሽ እና አስተያያት እንዲሰጡ ከሃያ አንድ (21) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡

መ ) ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ያገባኛል ከሚሉ ወገኖች አስተያየት ከተቀበለ በኂላ በተቀበለው አስተያየት ላይ ምላሹን ከሃያ አንድ (21) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በምላሹም፤

i. ለእያንዳንዱ አስተያየት ምላሽ በመስጠት የመጨረሻ ውሳኔውን ያሰፍራል፤ወይም
ii. ለእያንዳንዱ አስተያየት ምላሽ በመስጠት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቀረበው ሃሣብ ላይ ማሻሻያ በማድረግ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች በመጀመሪያው ዙር በተቀመጠው ተመሳሳይ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንደገና አስተያየት እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡

ሠ) ባለሥልጣኑ የመጨረሻ ውሳኔውን ከመስጠቱ በፊት በራሱ ሥልጣን ከሁለት ለበለጡ ዙሮች በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች ማሻሻያዎች ወይም አስተያየቶች እንዲያቀርቡ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

ረ) በቀጥጥሩ ሂደት ባለሥልጣኑ በተቀበለው አስተያያት ላይ የሰጠውን ምላሽ እና የመጨረሻውን ውሳኔ በድኅረ ገጹ ማውጣት ይኖርበታል፡፡

ሰ) በቁጥጥሩ ሂደት በጉዳዩ ያገባኛል በሚሉ ወገኖች ለባለሥልጣኑ የተሰጡ መረጃዎች ሚስጥራዊ እስከሆኑ ድረስ ባለሥልጣኑ የመረጃዎቹን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለበት፡፡

9) የአቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎቶች የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች፥ የቴክኒክ ደረጃዎች እንዲሁም በሮሚንግ አገልግሎት አቅራቢ የሚተገበሩ የደህንነት ደረጃዎች ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡

10) የአቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ የአገልግሎቱ የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች እንዴት እንደሚሻሻሉ የሚገልጽ ድንጋጌዎችን ማካተት አለበት፡፡

11) የአቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፦

ሀ) የስምምነት ማዕቀፍ፤

ለ) የሚቀርቡ የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ  አገልግሎቶች መግለጫ እና ተያያዥ የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች፤

ሐ) የበብሄራዊ ሮሚንግ ሽፋን የሚሰጣቸው ዝርዝር ቦታዎች

መ) ቴክኒካዊ ዝርዝሮች፣

ሠ)  የአገልግሎት አሰጣጥን፣ዕቅድን እና ጥገናን ጨምሮ የአሠራር ሥርዐቶች፤

ረ) ክፍያዎች፣ የክፍያ መጠየቂያ ሥርዐቶች እና የውል ቃሎችና ሁኔታዎች ጨምሮ ንግድ ነክ ጉዳዮች እንዲሁም የመሬት ኪራይ ወጪዎች፥ የማጠናከሪያ ስራዎች እና ሌሎችም

ሰ) የአገልግሎት ደረጃ ስምምነት፣

ሸ) የመረጃ ልውውጥን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንዲሁም ለተቀጥላ አገልግሎቶች የቴክኒክ መስፈርቶች እና

ቀ)  የአሰራር ስርሃቶችን ለማሻሻል የሚረዱ ድንጋጌዎችን

## <u>ክፍል ስድስት</u>
## <u>የብሔራዊ ሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት ክፍያዎች</u>

### 17.<u>የብሔራዊ የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት ክፍያዎች</u>

1) ለሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎቶች የሚጠየቁ ክፍያዎች፦-

ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 (1) በተመለከቱት መርሆዎች መሠረት የሚመሩ፤

ለ) በአዋጁ አንቀጽ 45 ፣ በዚህ መመሪያ እና በባለሥልጣኑ በጸደቀ ማናቸውም ተግባራዊ በሆኑ መመሪያዎች መሠረት ሕጋዊ የሆነ፤ እና

ሐ) በአዋጁ አንቀጽ 48 ፣በባለሥልጣኑ በቴሌኮሙዩኒኬሽን ሕጋዊ ታሪፍ መመሪያ ቁጥር 8/2013 እና  በቴሌኮሙኒኬሽን ውድድር መመሪያ ቁጥር 9/2013 መሠረት ፀረ-ውድድር ያልሆኑ፤ መሆን አለባቸው።

2) የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አገልግሎት ሕጋዊ ታሪፎች-

ሀ) ወጪ-ተኮር  እና

ለ) አለአግባብ አድሎ የማይፈጥሩ፤  መሆን አለባቸው።

3) የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ወጪ-ተኮር ታሪፎች ወደፊት እየጨመረ በመሄድ ወጪ ዘዴ ላይ መመስረት አለባቸው። የሚከተሉት መርሆች ለሮሚንግ ጅምላ ሽያጭ ዘዴዎች ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ፦

ሀ) ወደፊት እየጨመረ የሚሄድ ወጪ ማለት አንድ ውጤታማ ኦፕሬተር የተወሰነ አገልግሎት ለማቅረብ የሚያወጣውን ወጪ ይመለከታል።

ለ) የወጪ መሠረት የሚከተሉትን የወጪ ዘዴዎችን በመጠቀም ይቀመጣል-

i. በረጅም ግዜ እየጨመረ የሚሄድ ወጪ፤;
ii. ተደማሪ በረጅም ግዜ እየጨመረ የሚሄድ ወጪ ይህም (የጋራ እና መደበኛ ወጪዎችን ያካትታል)፤ ወይም፣
iii. ከችርቻሮ ዋጋ በታች።

4) ለሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ የተቀመጡ ታሪፎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 (1) መሠረት አለአግባብ አድሎ የሚፈጥሩ መሆን የለባቸውም። ይህ ማለት የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ አቅራቢ ለሞባይል ኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች የሚያቀርበው የችርቻሮ ታሪፍ እና የአገልግሎቱን አዲስ ፈቃድ ላለው ኦፕሬተር የሚያቀርብበት የሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት አንድ ውጤታማ ፈቃድ ያለው ኦፕሬተር በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ የሞባይል ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በመስጠት መዝለቅ የሚያስችለው መሆን ይኖርበታል።

5) ለሮሚንግ የጅምላ ሽያጭ የተቀመጠ ታሪፍ የህዳግ ጥበት ከፈጠረ ወይም የመፍጠር እድል ካለው ባለሥልጣኑ ባወጣው የቴሌኮሙኒኬሽን ውድድር መመሪያ ቁጥር 9/2013 መሠረት ፀረ-ውድድር ተግባር እንዳለ ተደርጎ ይቆጠራል።

6) ለሮሚንግ ጅምላ ሽያጭ የተቀመጡ ታሪፎች በሚከተለው መልኩ መለየት እና በተናጠል መታየት አለባቸው፡

ሀ) የሮሚንግ ጅምላ ሽያጭ አገልግሎት ለማቋቋም እና ተግባራዊ ለማድረግ ቋሚ የአንድ ጊዜ ክፍያ፤

ለ) ለመጠቀም የሚወጣ ወቅታዊ የኪራይ ክፍያዎች፣ እና

ሐ) ለተጨማሪ አገልግሎቶች የሚወጡ ተለዋዋጭ ክፍያዎች።

7) የሮሚንግ የጅምላ ታሪፎች የተሰጠውን የአገልግሎት ዓይነት መሰረት በማድረግ የሚከፈሉ ይሆናሉ። ይህም፦በዚህ መልኩ መከፈል አለባቸው -

ሀ) የድምፅ አገልግሎት በደቂቃ ይከፈላል ፣

ለ) የሞባይል መልእክት አገልግሎት (አጭር የጽሁፍ መልክት እና አጭር የቪዲዮ መልክት) በአገልግሎት አቅም ልክ ወይም በፅሁፍ መልእክት ብዛት እንዲከፍሉ ይደረጋል፤ እና

ሐ) በተዋዋይ ወገኖች የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ የዳታ የአጠቃቀም መጠን ወይም በአገልግሎት አቅም ልክ መሠረት እንዲከፈል ይደረጋል።

8) የሮሚንግ የጅምላ አገልግሎት አቅራቢ የሮሚንግ የጅምላ ታሪፎች እንዲጸድቁለት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።

9) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 መሠረት የሚቀርብ ማንኛውም ታሪፍ በባለስልጣኑ እስኪጸድቅ ድረስ ተፈጻሚነቱ እንዲዘገይ በአዋጁ አንቀፅ 45 (4) መሠረት ለሮሚንግ የጅምላ አቅርቢ ትህዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

10) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 መሠረት የሮሚንግ የጅምላ ታሪፎች ለማፅደቅ የቀረበን ጥያቄ በተቀበለ በሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ምላሽ ይሰጣል ፤ በምላሹም፦

ሀ) የቀረቡ ታሪፎችን ያጸድቃል፤

ለ) የቀረቡትን ታሪፎች ውድቅ ያደርጋል ፤ ወይም

ሐ) ታሪፉ ህጋዊ መሆኑን ለመገምገም እና ለማረጋገጥ በአዋጁ አንቀጽ 45 ፣ በዚህ መመሪያ እና የአዋጁን ከአንቀጽ 35 እስከ 38 የተደነገጉትን አሰራሮች ተከትሎ ባለሥልጣኑ ያፀደቀውን መመሪያ ወይም ማንኛውም ተፈጻሚነት ያለውን መመሪያ መሰረት በማድረግ የቁጥጥር ሂደት ለመጀምር ያሰበ መሆኑን ያሳውቃል።

11) ባለሥልጣኑ እንዲጸድቁ የቀረቡለትንታሪፎች በሠላሳ (30) የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልሰጠባቸው፤ ታሪፎች እንደፀደቁ ይቆጠራሉ።

12) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀፅ 8 እስከ 11 ላይ የተደነገገው ቢኖርም ባለሥልጣኑ በራሱ ውሳኔ በማንኛውም ወቅት ለሮሚንግ ጅምላ አገልግሎት የተቀመጠ ታሪፍ በአዋጁ አንቀጽ 45 እና 48፣ በዚህ መመሪያ ወይም ባለሥልጣኑ ካፀደቀው ማንኛውም መመሪያ ጋር የተጣጣመ እንደሆነ ለማረጋገጥ የግምገማ ሂደት ሊጀምር ይችላል።

## 18. <u>የሂሳብ ደብተር መለያየት</u>

1) ባለሥልጣኑ የሮሚንግ የጅምላ አገልግሎት አቅራቢን ለሞባይል ተደራሽነት እና የጥሪ መነሻን በተመለከተ አግባብነት ባለው ገበያ ውስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው ከወሰነ እና አገልግሎት

ሰጪው የችርቻሮ አገልግሎት የሚሰጥ በተዋረድ የተቀናጀ ኦፕሬተር ከሆነ ከአገልግሎቱ ጋር የተያያዙ ገቢ እና ወጪዎችን መለየት እንዲቻል በሕግ ራሱን ችሎ እንደሚሰራ ኩባኒያ የጅምላ ሽያጩን የተለየ የሂሳብ መዝገብ መያዝ አለበት፡፡

2) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የሂሳብ አያያዝ እንዴት ተግባራዊ መደረግ እንዳለበት የሚያሳይ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት
## አለመግባባት አፈታት

### 19.ብሔራዊ የጅምላ የሮሚንግ አገልግሎቶች አለመግባባት አፈታት

1) በቴሌኮሙዩኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል የጅምላ ሮሚንግ አገልግሎት ጥያቄን ምክንያታዊነት የሚመለከት ማንኛውም ክርክር ሲነሳ ወይም ተዋዋይ ወገኖች የጅምላ የሮሚንግ አገልግሎት ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ወይም በሌላ መንገድ የጅምላ የሮሚንግ ስምምነትን ተግባራዊ ማድረግ ካልቻሉ፤ ጉዳዩ ውሳኔ እንዲያገኝ በተዋዋይ ወገኖች በአንዱ ጥያቄው ለባለስልጣኑ ሊቀርብ ይችላል፡፡

2) ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉበት ከሰላሳ (30) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አለመግባባቱን እንዲፈታ የሚጠይቅ ተዋዋይ አካል ለባለስልጣኑ በጽሑፍ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡

3) የጅምላ የሮሚንግ አገልግሎት ስምምነት ተጥሷል ወይም ያለአግባብ ተቋርጧል ብሎ የሚከራከር የጅምላ የሮሚንግ ስምምነት ውል አካል የሆነ ወገን ባለሥልጣኑ በዚህ ክርክር ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ መጠየቅ ይችላል፡፡ በምንም ዓይነት ሁኔታ አለመግባባቱ በመፈታት ሂደት ላይ እያለ በየትኛውም ወገን የሮሚንግ አገልግሎት መቋረጥ አይኖርበትም፡፡

4) ባለሥልጣኑ በጽሑፍ የቀረበውን ጥያቄ ተከትሎ ይህን ጥያቄ በተቀበለ ከአስር (10) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለጠያቂው አካል ምላሽ ይሰጣል ፣ በዚህም ፡

ሀ) ጣልቃ ለመግባት ከመወሰኑ በፊት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ተጨማሪ መረጃ የሚፈልግ ከሆነ ይህኑ ያሳውቃል፤ ወይም

ለ) ጣልቃ ላለመግባት ከወሰነ ፤ ጣልቃ ላለመግባት እንዲወስን ያስቻለውን ምክንያት በጽሁፍ ምላሽ ይሰጣል ፣ ወይም

ሐ) በባለሥልጣኑ አለመግባባት አፈታት መመሪያ ላይ በተቀመጠው አሠራር መሠረት ጣልቃ ለመግባት ወስኖ እንደሆነ ይህኑ ያሳውቃል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ሕግ ማስፈጸም እና ሕግ ማክበር

### 20.ሕግ ማክበር

ባለሥልጣኑ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሰረት የሮሚንግ አገልግሎት አቅራቢ እና የሮሚንግ አገልግሎት ጠያቂን ሕግ ማክበራቸውን ይከታተላል፡፡

### 21.ሕግ ማስፈጸም

1) ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ፥ አዋጁ እና ባለስልጣኑ ያጸደቃቸውን መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ የሮሚንግ አቅራቢ ወይም የሮሚንግ ጠያቂ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ጥሷል ብሎ ከወሰነ፤ በአዋጁ አንቀጽ 52 መሰረት እርምጃ የሚወስድ ሲሆን እርምጃው የገንዘብ ቅጣት ወይም ካሳ ሊሆን ይችላል፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ የሚወስደው እርምጃ እና ቅጣት የሚመራው በአዋጁ አንቀጽ 52(6) መሰረት የሚንስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ሲሆን በዚህ ደንብ የትኞቹ መተላለፎች የፈቃድ መሰረዝ፥ መታገድ እና ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንደሚያስከትሉ የሚያመለክት ሲሆን ቅጣቶችን ለይቶ የሚያስቀምጥ እና የሚጣለው የመቀጮ ገንዘብ መጠን ይወስናል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ

### 22.ማሻሻያ

ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አስቀድሞ ለሁሉም ባለፈቃዶች በማስታወቅ እና በአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት የባለድርሻ አካላትን የምክክር ሂደት በማካሄድ በማንኛውም ጊዜ ይህንን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

### 23.ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 2 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 2 ቀን 2013 ዓ.ም**

**ኢንጂነር ባልቻ ሬባ**
**ዋና ዳይሬክተር**
**የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን**